## ምዕራፍ 1 ፡ ምንባብ ሁለት ፡ ጓደኛ መሆን

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛውን ምላሽ ስጡ

1. በምንባቡ ውስጥ ስለጓደኝነት በዋናነት ምን ተማራችሁ ?

ሀ) ታጋሽነትን　　　ለ) ይቅርባይነትን

ሐ) ንዴትን　　　መ) ሀ እና ለ

2. አንዳንድ ጨዋታ በድካም መንፈስ ከተጫወቱት **ለጠብ** ይዳርጋል፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍቺ .....

ሀ) ለመዋደድ　　　ለ) ለመጣላት

ሐ) ለረሃብ　　　መ) ለ እና ሐ

3. ‹‹ ***የድካምና የእረፍት ጨዋታ ለየቅል ነው*** ›› ሲባል ምን ለማለት ነው ?

ሀ) በድካምም በእረፍትም ጊዜ መጫወት ጥሩ ነው

ለ) በድካም ጊዜ እና በእረፍት ጊዜ የሚደረጉ ጨዋታዎች መለያየት አለበት

ሐ) በድካም ጊዜ መጫወት ጥሩ አይደለም

መ) የእረፍት ጊዜ ጨዋታ ከድካም ጊዜ ጨዋታ ይበልጣል

LIVEWORKSHEETS

4. «ዛሬ እጅግ የምወደው ጓደኛዬ ሕይወቴን ከሞት **<u>ታደጋት</u>**» ብሎ ጻፈ፡፡ ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ) አገዘው ለ) አዳነው

ሐ)መለሰው መ) ለየው

5. ጓደኝነትን ለረዥም ጊዜ ለማስቀጠል ምን መደረግ አለበት ?

ሀ) መቻቻል፣ መታገስ እና ንዴትን መቆጣጠር ለ) ጥፋት ሲጠፋ ይቅርታ መደራረግ

ሐ) በጓደኝነት መካከል የሚፈጠሩ ክፉ ነገሮችን ሳይሆን መልካም ነገሮችን አዘውትረን ማስታወስ

መ) ሁሉም

6. ***‹‹መንገድ በዝምታ ይረዝማል***›› ማለት ምን ለማለት ነው ?

ሀ) እየተጨዋወቱ ከሄዱ መንገዱ ሳይታወቀን ያጥራል

ለ) ሳይጨዋወቱ ዝም ብሎ መሄድ መንገዱን ለዥም ያደርገዋል

ሐ) ሳንጨዋወት ዝም ብለን ከሄድን መንገዱ ያሰለቸናል/ አያልቅልንም

መ) ሁሉም

7. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የትዕግስትን አቅም የሚፈታተነው ምንድን ነው?

ሀ. ይቅር ባይነት ለ. ድካም ሐ. እልኸኛነት መ. ረሀብ

8. በቡጢ የተመታው ልጅ ማዘኑን የገለጸው ምን በማድረግ ነው?

ሀ. አንገቱን በማወዛወዝ ሐ. አሸዋ ላይ በመጻፍ

ለ. በማልቀስ መ. ይቅርታ በመጠየቅ

9. ***‹‹ዛሬ እጅግ የምወደው ጓደኛዬ ግንባሬ ላይ በቡጢ መታኝ***› ብሎ የጻፈው ምን ላይ ነው?

ሀ. በድንጋይ ላይ ሐ. በወረቀት ላይ

ለ. በአለት ላይ መ. በአሸዋ ላይ

LIVEWORKSHEETS

10. በቡጢ የተማታው ልጅ ጓደኛው እግር ላይ የወደቀው ለምንድን ነው?

ሀ. እየሮጠ ሲሄድ

ሐ. ይቅርታ ለመጠየቅ

ለ. ጓደኛው በቡጢ ስለመታው

መ. ጓደኛውን ለመጣል

11. ጓደኛሞቹ ልብሳቸውን አውልቀው ወደ ወንዝ የገቡት ለምንድን ነው?

ሀ. ውሃ ለመጠጣት

ሐ. ዋና ስለሚወዱ

ለ. ስለደከማቸው

መ. ልብሳቸውን ለማጠብ

12. የአንቀጽ ***ሶስት*** ዋና ኃሳብ ምንድን ነው ?

ሀ) በባልጩት ድንጋይ ላይ ስለመፃፍ

ለ) ጓደኛውን ከሞት ስለታደጉ

ሐ) አንደኛው ልጅ በቡጢ ስለመመታቱ

መ) በቡጢ ስለተመታው ልጅ ንዴት

13. የአንቀጽ ***አራት*** ዋና ኃሳብ ምንድን ነው ?

ሀ) የተመታው ልጅ ስለደረሰብት ጉዳት

ለ) ወንዝ ውስጥ የገባውን ልጅ ስለማዳን

ሐ) ክፉ ነገሮችን ስለመተው እና ጥሩ ነገሮች ላይ ትኩረት ስለማድረግ

መ) ለ እና ሐ

II. በ "ሀ" ረድፍ ያሉትን በ "ለ" ረድፍ ካሉት ጋር በማዛመድ ቁጥሩን በባዶ ቦታው ላይ አስቀምጡ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ጉልበት | ................ ሀ. ተመለከተ/ፈለገ |
| 2. እየተጫዋወቱ | ............. ለ. አቅም |
| 3. አማተረ | .............. ሐ. ጥጫ |
| 4. ብልጭ አለበት | .............. መ. እያወሩ |
| 5. ቡጢ | ............... ሰ. ተናደደ |
| 6. ባልንጀርነት | ............... ረ. ወዳጅነት |

LIVEWORKSHEETS